የOAH የተሻሻለ የአሰራር የጊዜ ሰሌዳ

OAH በተሻሻለ የአሰራር የጊዜ ሰሌዳ ቢያንስ እስከ ሜይ 15 ድረስ ክፍት ነው እና ሁሉም ሰራተኞች በስልክ ስራ ላይ ናቸው። ይህም ኤጀንሲው ጥቅማጥቅሞች ሲከለከሉ ወይም ሲቋረጡ ለህዝብ ጥቅማጥቅሞች ወይም የስራአጥ የመድን አመልካቾች/ተቀባዮች **በርቀት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ክርክሮች** እንዲዘጋጅ እና እንዲያካሂድ ይጠይቃል። እነዚህ ክርክሮች በድጋሚ የተጀመሩት ማርች 30፣2020 ባለው ሳምንት ነው።

**ሁሉም ሌሎች ክርክሮች፣ በከንቲባው አስቸኳይ ክርክሮች ተብለው ከተመደቡት በስተቀር፣ OAH አቅሙን እና መሰረተ ልማቱን ማሳደግ ሲቀጥል በቅድሚያ የፍቃድ እና የአፈጻጸም ጉዳዮች ላይ በማተኮር ቀስ በቀስ እየተጀመሩ ነው።**

**OAH እነዚህ ክርክሮች እንደገና ሲጀመሩ ተከራካሪ ወገኖች እነዚህን ማስታወቂያዎች እንዲያውቁት ያደርጋል። ነገር ግን፣ ሁሉም ክርክሮች ሌላ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ በቴሌፎን ይደረጋሉ።**

በተለይም፣ OAH የህዝብ ዘርፍ የሰራተኞች ካሳ ክርክሮችን ሜይ 1 ላይ እንደገና ይጀምራል።

ስለ ህዝብ ጥቅማጥቅሞች ጉዳዮች ተጨማሪ መረጃ በ(202) 671-0055 በመደወል ሊገኝ ይችላል።

በህዝብ ጥቅማጥቅሞች ጉዳይ ላይ አስቸኳይ ክርክር እንዲሰማ ለመጠየቅ የ OAH የኦንላይን ቅጽን መጠቀም ይችላሉ። የኦንላይን ቅጽ የሚገኝበት የአገናኝ መስመር በዚህ ገጽ ታች ላይ ይገኛል።

ስለ ስራአጥነት የመድን ጥቅማጥቅሞች ጉዳዮች ተጨማሪ መረጃ በ (202) 442-8175 በመደወል ማግኘት ይቻላል።

OAH በውስን አቅም የ DCRA ክርክሮችን እየሰማ ነው። ክርክር ስለሚሰማበት የጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ ካሎት፣ እባክዎ ይደውሉ ወደ (202) 724-4904 ።

ስለ ሁሉም ሌሎች ጉዳዮች ለተጨማሪ መረጃ፣ ይደውሉ (202) 724-4904 ።

OAH በስልክ የሚደረጉ ክርክሮች ብዙም ተመራጭ እንዳልሆኑ ይረዳል፣ ነገር ግን በዚህ ወረርሽኝ ጊዜ እርስበርሳችንን ለመጠበቅ ይህን መተው አይቻልም። ስለዚህ፣ እኛ በሚከተሉት መንገዶች የእርስዎን ትብብር እንጠይቃለን፣

- በወረርሽኙ ጊዜ መደበኛ ደብዳቤ የመላክ እና የመቀበል ችሎታ ሊገደብ ስለሚችል፣ እባክዎ ከ OAH ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነቶች ሁሉንም በኤሌክትሮኒክ መንገድ በ oah.filing@dc.gov ወይም ከላይ በተገለጹት የስልክ ቁጥሮች በመደበኛ የስራ ሰዓቶች፣ ከጥዋቱ 9 - ከሰዓት 5 ድረስ ለማድረግ ጥረት ያድርጉ።

- የሚቻል ከሆነ፣ የ OAH ሰራተኛ አስፈላጊ ሲሆን በፍጥነት እና በአግባቡ እንዲያገኝዎ፣ እርስዎ ሊገኙበት የሚችሉበትን የኢሜይል አድራሻ እና የስልክ ቁጥር ያካትቱ ።

- እርስዎ ሊገኙበት የሚችሉ የኢሜይል አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ከሌሎት ወይም ደግሞ መስጠት የማይችሉ ከሆነ፣ ለተጨማሪ እርዳታ እባክዎ እነዚህን ቁጥሮች ይደውሉ።

- እባክዎ ቴክኖሎጂው ፍጹም እንዳልሆነ እና የ OAH ሰራተኛ፣ ጉዳይዎን የሚያዩ የአስተዳደር ህግ ዳኞችን ጨምሮ፣ ሁኔታዎቹ ውጤታማ ለማድረግ የተቻላቸውን ያክል እየሰሩ መሆኑን ይረዱ። ስለዚህ፣ በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ትእግስትዎ እና ጥሩ ባህርይዎ በጣም ይደነቃል።